# ኢትዮጵያ

መስከረም/ ጥቅምት /2006 | 2ኛ ዓመት | በነፃ የሚሰራጭ



ሶፊያ አየለ በከፍተኛ 15 1970 ዓም በቅርብ ቀን በዴንቨር ኮሎራዶ ፍርድ ቤት ወንጀሉ በተረጋገጠዉ በከፍያለኝ አለሙ በግፍ የተገደለች

**ርእስ አንቀጽ ገፅ 2**

በአዲሱ ዓመት የነጻነታችን ዘመን ይጥባ

**ዜና ከተባለ ገፅ 3**

ከፉውን ደጉንም ሁሉንም
አይተናል ትላንት ዛሬ አይደለም
ምን ያስገርመናል ብሎ ዝማሪው
አሰምቶን፤አሳስቦንም ነበር

**ምን ይሰማ....... አገር ገፅ 3**

**ትላንትና ገፅ 5**

የቦረና ነጌሌዎቹ የኢሕአፓ ወጣቶች ሕዝባዊ ገድል በጨረፍታ ቅኝት

**ነፃ ሀሳብ ገፅ 6**

የማይፈርስ ምሽግ የማይወድቅ ጨቋኝ አገዛዝ የለም !

የኢትዮጵያ ጋዜጣን በተለያዩ ድረ ገጾች

**EPRP.COM**
**ASSIMBA.ORG**
**DEBTERAW.COM**
**ETHIOLION.COM**
**ወዘተ.**

- **FACE BOOK (ethiopianewspaper)**

## የቀይ ሽብሩ ተዋናይ፣ ከፈለኝ አለሙ፣ ጥፋተኛ ተባለ

በኦክቶበር 11፣ 2013 ዴንቨር ኮሎራዶ ውስጥ የተሰየመው ፍርድ ቤት፣ በቀይ ሽብር ወቅት በወጣቶች ላይ ሰቆቃ ሲፈጽም የነበረውን ከፈለኝ አለሙን፤ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ነህ ሲል ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዜና ያስረዳል፡፡

በዕለቱ የተሰየሙት ዳኛ፣ ከፈለኝ አለሙን፣ ማንነቱን በተመለከተ የአሜሪካንን መንግስት በማጭበርበሩ፣ በመዋሸቱና በቀይ ሽብር ወቅት ሰቆቃ በመፈጸም አልተሳተፍኩም ብሎ በማለቱ በሶስት ወንጀሎች ጥፋተኛ ነህ ብለውታል፡፡

ከፈለኝ አለሙ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ የ 22 ዓመት እስር እና እስሩን ከጨረሰ በኋላ ደግሞ የአሜሪካ ዜግነቱ ተነጥቆ ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ እጣ ፈንታ ሊጠብቀው እንደሚችል ተገልጾለታል፡፡

ፍርድ ቤቱ በከፈለኝ አለሙ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ዲሴምበር 19፣2013 ቀጠሮ መያዙንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከፈለኝ አለሙ የሌላ ሰው ማንነት ይዞ ከኬኒያ ወደ አሜሪካ በ 2004(እ.ኤ.አ) ዓ.ም የገባ ሲሆን፣ እስከ 2011 ዓ.ም፣ ዴንቨር የሚገኝና በቀይ ሽብር ወቅት አዲስ አበባ ከፍተኛ 15 እስር ቤት ውስጥ ያውቀው የነበረ ግለሰብ፣ "አንተ ከፈለኝ አለሙ አይደለህም እንዴ" ብሎ ካጋለጠው እና በአሜሪካ ፖሊሶች ተይዞ ፍርድ ቤት እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ በዴንቨር ኮሎራዶ የሌላ ሰው ስም በመያዝ ተደብቆ ሲኖር ቆይቷል፡፡

ከፈለኝ አለሙ እስከዛሬ በቀረበባቸው ችሎቶች ሁሉ እኔ ከፈለኝ አለሙ አይደለሁም ሲል የቆየ ቢሆንም በመጨረሻ ላይ ግን አቃቤ ህግ ያቀረባቸው ምስክሮችን የምስክርነት ቃል መቋቋም ባለመቻሉ "እኔ ከፈለኝ አለሙ ወርቁ ነኝ" የአሜሪካ መንግስትን የሌላ ሰው ማንነት በመያዝ አሳስቻለሁ...በማለት የእምነት ከህደት ቃሉን ለፍርድ ቤቱ በጽሁፍ ለመናዘዝ በቅቷል፡፡

አቃቤ ህግ በከፈለኝ አለሙ ላይ ምስክሮችን ያቀረበ ሲሆን ሁሉም ምስክሮች በቀይ ሽብር ወቅት አዲስ አበባ በከፍተኛ 15 እስረኛ የነበሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ምስክሮች ከፈለኝ አለሙ የገረፉቸውና ሰቆቃ የፈጸመባቸው ሲሆኑ በዛን ወቅት ከፈለኝ አለሙ በእስር ቤት ውስጥ በርካታ ወጣቶችን በአሰቃቂ ሁኔታ ሲገድል ፣ሲያሰቃይና ሲገርፍ መመልከታቸውን ለፍርድ ቤቱ ተራ በተራ ማስረዳታቸው ተዘግቧል፡፡

ከፈለኝ አለሙ ግን እኔ ባለስልጣን አልነበረኩም የተደረገውን ሁሉ የፈጸምኩት ታዝዤ ነው፤ ይህ የአሁኑ ድርጊት በኔ ላይ የተሰነዘረ በቀል ነው ሲል ተደምጧል፡፡ ይሁንና ለከፈለኝ አባባል ሁኔታውን ይታዘቡ ከነበሩ ወገኖች የተሰጠው መልስ የናዚ ወንጀለኞችም ይሉ የነበሩት ይሄንኑ ነበር የሚል ነው፡፡

በርካታ ወገኖች፣ እንደ ከፈለኝ አለሙ አይነት "የጦር ወንጀለኞች" ከየተደበቁበት እየተጋለጡ እፍትህ ፊት መቅረብና ፍርድ ማግኘት እንዳለባቸው አጥብቀው መናገራቸውን ከዴንቨር ኮሎራዶ የፍርድ ሂደት ለመረዳት ችለናል፡፡ ይህን ተከትሎም የአሜሪካ የፌደራል ባለስልጣናት በቀይ ሽብር ወቅት በንጹሀን ላይ ሰቆቃ የፈጸመ ነው ብለው የጠረጠሩትን ሌላ ሰው አትላንታ ውስጥ ይዘው ማሰራቸው መዘገቡ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ወንጀለኞች የትም ተደብቀው ከፍትህ እንደማያመልጡ የሚያሳይ ነው ሲሉ ታዛቢዎች መናገራቸውን የዴንቨር ኮሎራዶ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

## አቦይ ስብሀትና ኩልኮሎቹ
## ዋሽንግተን ዲሲን ወረሯት ፣ ተራወጡም።

ለኢትዮጵያና ለአንድነቷ ጸር በመሆን የሚታወቀውና በመቀላመድ ተወዳዳሪ የሌለው አቦይ ውሸት (ስብሀት ነጋ) በያዝነው ወር ውስጥ በዲሲ ከርሟል። ሀገር ለማሻሻጥ ሁነኛው ወያኔ ስብሀት ነጋ በገባበት፣ በወጣበት ባደረበት ሆቴል ጭምር የዋሽንግተን የተግባር ግብረ ኀይሎች ሲያራውጡት ከርመዋል። በክርስቲያል ሲቲ ከከተማ ሀያት ሆቴል በተከታታይ ሁለት ቀናት በዶፍ ዝናብ ተሰልፈው የሰውየውን አራዊትነት ለህዝብ አጋልጠዋል አሳድደውታልም። ከ30 በላይ የሚሆኑ ሰልፈኞችም የማስጠንቀቂይ ቲኬት ከፓሊስ ተስጥቷቸዋል። ግን አቦይ ውሸትን ክፍኛ አራውጠውታል። በዚያኑ ሰሞን ለገንዘብ ማጋበስ ከኢትዮጵያ ተንደርድረው የመጡ ቱባ የወያኔ ባለስልጣኖች ኢትዮጵያውያን ሰልፈኞች ያለም ባንክን አጥለቅልቀው ብሶት በማሰማታቸው የቋመጡለት ብድርና ርዳታ ተከልክዋል። በዚሁ ባሳለፍነው ወር ይኸው የኢትዮጵያ ጠር የሆነውን አቦይ ውሸት ነጋን ጋዜጠኛ ሳድቅ መሐመድ በድምጻችን ይሰማ መፈክር ስብሐትን እንደመለሰ አንገቱን አስቆልምሞታል። የቀረው ግን እንደመለስ ጉዞው ብቻ ነው ይላሉ።

******

## የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ(የኢፓእአኮ) ባዘጋጀው ለጠፉ እስረኞች ምሽት በከፍተኛ ድምቀት ተከበረ

ባሳለፍነው አክቶበር 8 በካናዳ ዊኒፔግ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ(የኢፓእአኮ) ባዘጋጀው ለጠፉ እስረኞች ምሽት በከፍተኛ ድምቀት የተለያዩ ሀገራት የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችና ታዳሚዎች በተገኙበት ለሰባተኛ ጊዜ በድምቀት መከበሩን የገለጹልን የኢፓእአኮ ፕሬዝዳንት አቶ አሊ ሁሴን ነበሩ። ዜናውም በካናዳ ታዋቂ መገናኛ ብዙሀኖች መደመጡና መታየቱ ታውቋል።

*****

## የወያኔው ሌተናል ጄነራል ወደ ስዊድን ኮበለለ።

የወያኔው ሌተናል ጄነራል ገዛሂ አብራ ቤተሰቦቹን ሰብስቦ ወደ ስዊድን ኮበለለ። ይህ ግለሰብ በሱዳን አብዬ ግዛት ውስጥ የሰፈረውን የሰላም አስከባሪ ኀይል ተብዬውን እንዲመራ በህዋት ተመድቦ ይሰራ እንደነበር ይታወቃል። በተጨማሪም ሟቹ ጥ/ ሚንስቴር መለስ ዜናዊ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ለመከለከያ ምክር ቤት ለ25 ከፍተኛ የህዋት መኮንኖች በሽልማት መልክ 500 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው አንደኛ ደረጃ የሆነ መሬት እንድሰጣቸው ያስተላለፈውን ትእዛዝ ተከትሎ በነጻ ባገኘው መሬት ቤት ሰርቶ በውር 170 ሺ በር ያገኝ እንደነበር ታውቋል።

## መለስ ከሞተ ወዲህ በአንድ ዓመት ውስጥ 70 ጄኔራል መኮንኖች ተሾሙ

በወያኔ ቡድን ውስጥ የተፈጠረውን የኃይል አሰላለፍ ተከትሎ የነ ሳሞራ የኑስ ቡድንን የበላይነትን የሚያጠናክር አዲስ የማዕረግ እድገት ተሰጠ፡፡

አንዴ ሲወጠር ሌላ ግዜ ሲረግብ የነበረው በወያኔ ቡድን ባለስልጣናት እና በጄነራል መኮንኖች መሀከል የተፈጠረውን ሽኩቻ ለማርገብና ጨርሶ ገና ስልጣን ላይ ከወጣ አንድ ሳምንት ባስቆጠረው በአህዴዱ ዶ/ር ተሾመ ሙላቱ ፊርማ በሳሞራ የኑስ አቅራቢነት 28 ኮሎኔሎች ተበዎች የብርጋዲየር

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል**
**የሚዘጋጅ ወራዊ ጋዜጣ**



አድራሻ፡ 5309 Georgia Ave. NW 2nd floor Washington DC. 20011
ስ/ቁ፡ 202 291 4217
ኢሜል፡ dc..region.eprp@gmail.com


## ርዕሰ አንቀጽ

## በአዲሱ ዓመት የነጻነታችን ዘመን ይጥባ

በራሳችን የዘመን አቆጣጠር ፤ ኢትዮጵያዉያን "ኢዮሃ" በሚል ዝማሬ የምንቀበለዉ አዲስ ዓመት ከባተ ቀናት ተቆጥረዋል ። በየዐዉደ ሕይወቱ በነፍስ ወከፍም ሆነ በወል ጥረት የተቀዳጀናቸዉ ዉጤቶችም ተጠረቃቅመዉ ታሪክ ሆነዉ ሊመዘገቡ ከአሮጌዉ ዘመን ጋር አልፈዋል ።

እያንዳንዱን አዲስ ዓመት ብሩህ ተስፋን ባዘለና ባንሠራራ ስሜት መቀበል የሰዉ ልጆች በሙሉ የሚጋሩት ይትበሃል ነዉ። ይሁን እንጂ ፤ ከአራት አሥርት በላይ ላስቆጠረ ጊዜ በየአዲሱ ዘመን መግቢያ ፤ፍትሕ እኩልነትና ነጻነት ለተረጋገጠበት ማኅበራዊ ዕድገት የሰነቀዉን ተስፋ ደጋግሞ ለተነጠቀና ሰቀቀንን ታቅፎ ለከርሞ ለበቃዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የምኞት ፈረስ ብቻዉን ዳር እንደማያደርሰዉ ግልጽ ነዉ። በመሆኑም አዲሱን ዘመን አስመርኩዘን የምናስተላልፈዉ መልዕክት በዉብ ቃላት የተከሸነ ምኞት የሚያርከፈክፍ እንዲሆን አይጠበቅም ። በምትኩ እንደ ሕዝብና እንደ ሀገር ከላዩ ላይ እንደመርግ የተጫነዉን ዘረኛ ሥርዓት ከሥሩ መንግሎ ከመጣል ያገደዉን ጠጣሩን ድክመት ለመሸብለቅ የላላዉን አንድነቱንና ትግሉን አፈርጥሞ ማጠንቸት እንደሚገባዉ በአንክሮ ማሳሰብ ተገቢ ይሆናል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አምባገነናዊዉን አገዛዝ ለማስወገድ ከተያያዘዉ ትግል አኳያ ያለፈዉ የ፪፻፭ ዓ.ም አንጻራዊ ስኬትና አዎንታዊ ሁነቶች ተመዝግበዉበታል ። ሥርዓቱ ከምንጊዜዉም በላይ በዉስጣዊ ቅራኔዎቹ ተወጥሮ አለመረጋጋቱ በይፋ እየታየ ነዉ ። የኑሮ ዉድነትና የገንዘብ ግሽበት ፤ ሥራና መጠለያ አጥነት ፤እንዲሁም የተንሰራፋዉ ሙስና ፤ የዜጎች ማኅበራዊ ሕይወት በአስከፊ ደረጃ ለመቃወሱ ጉልህ ማሳያዎች ሆነዋል ። የዚያኑ ያህልም የአገዛዙን መደፈር በሚያመለክት መልኩ ኢትዮጵያዉያን በተለያየ አቅጣጫ ብሶቶቻቸዉን ለማስተጋባት ወደ አደባባዮች መትመም ጀምረዋል ። በዚህ ረገድ የእስልምና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዉያን መብታቸዉን ለማስከበር የሚያደርጉት ትግል ለሁለት ዓመታት ተጠናክሮ መዝለቁ ጎልቶ ሊጠቀስ የሚገባው ክንዋኔ ነዉ ።

እነዚህ ዉጤቶች መንግሥታዊዉን አፈናና ወከባ ብቻ ሳይሆን ወያኔና ደቀመዛሙርቱ በሕዝቡ መሃከል ጥላቻን ለመዝራት ሌት ተቀን የሚያደርጉትን መርዛማ ሤራ በመቋቋም የተገኙ ናቸዉ ። የሕይወት ዋጋም ተከፍሎባቸዋል ። ሰላማዊ የኅብረተሰብ አባላት መብታቸዉ እንዲከበር በጠየቁ ፤ጋዜጠኞች እዉነቱን በዘገቡ፤ በአሸባሪነት ተፈርጀዉ ወህኒ ወርደዋል ። አገር ጥለዉ ተሰድደዋልም። በዚህ ደረጃዉ ሕዝቡ እያደረጋቸዉ ያሉት የተቃዉሞ እንቅስቃሴዎች የሚያበረታቱ በጎ ጅማሬዎች መሆናቸዉ አያከራክርም ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከአድማስ አድማስ የሚያንዣብበዉን የመከራ ደመና ለመግፈፍም ሆነ የወያኔን አገዛዝ በመገርሰስ በሥፍራዉ ልናቆመዉ የምንሻዉን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት ብቁ አይደሉም ። ትግሉ ጠላትን ብርክ በሚያስይዝ መልኩ ተጠናክሮ ለላቀ ዉጤት ይበቃ ዘንዳ እስካሁን ያለዉ የተቃዉሞ እንቅስቃሴ ጎልብቶ ወደሚቀጥለዉ የሕዝብ አመጽ ደረጃ መሸጋገር ይኖርበታል ። የሙስሊም ኢትዮጵያዉያን የመብት ትግል ከክርስትያኑ ወገን መሰል ተግባር ጋር ሊቀናጅ ፤ የመብት መጠየቂያዉ ሰልፍም ወደ መብት ማስከበሪያ ትንቅንቅ እርከን ማደግ ይኖርበታል ።

በሀገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች አሰላለፍ ረገድም የተፈረቀቁ መስመሮች መጠጋጋትና ወደአንድ አቅጣጫ መምጣት ይጠበቅባቸዋል ። ኢትዮጵያን ከዉድቀት አፋፍ ለማዳንና ለወደፊቱም ከመሰል የመበታተን አዙሪት ለማስጣል እንዲቻል ጉዳዩ ያገባናል የሚሉቱ የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይሎች በጠንካራ ህብረት ተሰናስለዉ ከፍልሚያዉ የመጀመሪያ ረድፍ ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል ።የዚያኑ ያህልም ፍትህ እኩልነትና ነጻነት ለሰፈነባት የጋራ ሀገር ባለቤትነት ዜጎች ካላቸዉ ህልም የተፋቱ ፍላጎቶችን ፤ እንዲሁም ሕዝባዊዉን ትግል የሚያሰናክሉ ከመስመር ያፈነገጡ አዝማሚያዎችን በንቃት መታገል ይጠበቅባቸዋል ።የአገርን ህልዉናና መጻዒ ዕድሏን በተመለከተ የሕዝቡ ፈቃደኛነትና ተሳትፎ ለአፍታም ያህል እንኳ ቸል የማይባል ግብዐት መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል ።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል/
በነጻነቷ ኮርታ፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር /

## ደብዳቤዎች

ውድ የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች
እንደምን ናችሁ? ጋዜጣችሁን እየተከታተልኩ አነባለሁ። ዛሬ ለናንተ ይህን መልእክት እንድልክ የገፋፋኝ ጉዳይ ከወዳጄ ጋር ስታር ፔንታጎን ሲቲ በሚገኝ ባር ቁጭ ብለን ሰሞኑን በዋሽንግተን ዲሲ ስለሚነዛው ውዥንብር አንስተን ስንጨዋወት፤ ጓደኛዬ "ይሁን እባክህ ለበጎ ነው። ካልደፈረሰ አይጠራ ይባል የለ! በቅርቡ ይጠራል ወያኔም ይወድቃል። " አለ። የጓደኛዬ የሥራ ሰዓት ስለደረሰ፤ ጨዋታችንን በዚሁ በመቋጨት መለያየት ግድ ስለነበር ተሰነባብትን።

አይ ጉድ ካልደፈረሰ አይጠራም አለኝ በማለት ሁኔታው እያሰላሰልኩ ወደቤቴ ለመመለስ ባቡር ላይ ተሳፈርኩ። ለወትሮው በባቡር ስጓዝ አልፎ አልፎ የተጓዡን ሁኔታ እየታዘብኩና የሚነበብ ነገር ከያዝኩ ያንን እያነበብኩ ነበር የምጓዘው። የዛሬው ጉዞዬ ግን ለየት ያለ ነበር። በሀሳብ የተመጠመደ ጉዞ!

ካልደፈረሰ አይጠራም!!! የዲሲ አየር ከተበከለ ውሎ አድሯል። እስከመቼ የተበከለ አየር እየተነፈስን እንኖራለን? አንዱ ከኔ በላይ ፀረ-ወያኔ የለም ብሎ ሲደንፋ ይቆይና ሳይታሰብ ጭልጥ ብሎ የጠፋል። ሌላው ደግሞ ወያኔን ሲያወግዝ ይከርምና ሳይታሰብ እጥፍ ይልና እንደወያኔ ያለ ቅዱስ መንግስት በዚህ ዓለም ሊመሠረት አይችልም፤ ይልቁንስ ተባብረን አገር እናልማ። አገር ቤት ሄደን ኢንቬስት እናድርግ ብሎ ከመስበክም አልፎ ወደ አገር ቤት ይሄዳል፤ ካመቸው እዚያ ይለምዳል። ከወያኔም ጋር ፍቅሬ ፍቅሬ በዛ ይላል። አላቅርብ ካሉት ወይም የሚፈልገውን ካላገኘ በድጋሚ ከአገር ወጥቶ ወያኔን በጦር ካልሆነ በሌላ አይቻልም በማለት ሳያፍር አላፊ አግዳሚውን ለመስብክ ይቃጣዋል።

አንዳንዱ ሳያሳናበት ለረጅም ጊዜ ከአየር ላይ ከጠፋ በኋላ ድንገት ብቅ በማለት ከኔ ወዲያ የሀገር ፍቅር ያቃጠለው፣ ከኔ ወዲያ ጋዜጠኛ የለም ማለት ሲከጅለው፤ ሌላው ደግሞ እንደኔ ያለ አገር ወዳድ ምሁር፣ የፓለቲካ አዋቂ የለም በማለት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲለፍፍ ማዳመጥ የተለመደ ሆኗል። ምን ይህ ብቻ ድርጅቶች እንደባክቴሪያ እየተራቡ በዋሽንግተን አካባቢ ለሚገኘው መቶ ሺ ሰው መቶ ሺ ድርጅት ሊኖረን ነው። ሞክሼ ድርጅቶችም በዚያ መጠን ያለ ሀፍረት እየተራቡ ነው። አዬ ጉድ!መውረጃዬ ደሬሰ። እናንተስ ምን ትሉ ይሆን?

ይታያል እውነቱ
ከሲልቨር ስፕሪንግ ሜሪላንድ

ኢትዮጵያ ጋዜጣ

ጥሩ ታዝበዋል። ባለንበት አካባቢ አንዳንዶች አፈ ጮሌዎች ሁሉንም መሆን የሚችሉበት ዘመን እንደመጣላቸው ሊነግሩን እየሞከሩ ነው። ፓለቲካ ማለት ሳይንስ መሆኑ ቀርቶ፤ ውሸት፣ ሽወዳ፣ ፓለቲከኛም አዋቂ፣ እውነተኛ፣ አገር ወዳድ መሪ መሆኑ ቀርቶ ጮሌ፣ ውሸታም፣ ቀላማጅ ነው እያሉን አይደል?



# ዜና ከተባለ

**መስተዋት ከደሬ**

**ከፉውን ደጉንም ሁሉንም አይተናል**
**ትላንት ዛሬ አይደለም ምን ያስገርመናል ብሎ**
**ዝማሪው አሰምቶን፤አሳስቦንም ነበር ።**

ለ እኛ ችግር የሆነው ግን ትላንት የዛሬ እጮኛ ሆኖ አልለቅ አልሄድ ማለቱ ነው ። በሰሞኑ የ ኤርትራው ወጠምሻ ለምን ዜጎቹ በላምፓዱሳና ሌሎች ቦታዎች ሸሽተውት ተሰደው እንደሚያልቁ መናገር ሲገባው ኢትዮጵያ ሀገር ከሆነች ( ጭፋራዎቹ መቶ የሚሉት በዝቶበት) 50 ዓመት ቢሆን ነው ብሎ የትላንቱን አብዝቶት ለፍፏል ። ይህም ያስገረማቸው አሉ፡፤ ጸረ ኢትዮጵያ መሆኑን ካስመስከረ፤ አማራን ክላጠፋሁ ብሎ ቧራቂው፤ ዋሾው፤ ባለጌና ዋልጌው ስብሐት ነጋም የጥጋቡ ጥጋብ በዓሜሪካ መሬት በጠገቡ ጠባቂዎቹ አንድ ዜጋ ላይ ካስተፋም ኋላ በሰጠው ቃለ መጠይቅ የሻዕቢያ ዋና ጠበቃ ሆኖ መለፈፉ ዓሁንም ያስገረማቸው አልጠፋም ። ስብሓት ጸረ ኢትዮጵያ ግን ይህን ሲለፍፍ ዓመታት አልፈዋል ። አዲስ ነገር ሁሉም አልተናገሩም ግን አልሰማ ያሉ ጆሮዎች ናቸው ወይ ጉድ ሰማን እኮ ብለው የሚገረሙትና የሚደናገሩት። ሁለት ብለን ወደ ሶስት ስንጓዝ ደግሞ የወያኔና የሻዕቢያ ዋና መሰሪና ቅጥረኛ ሆኖ የባጀውን ደራሲና ጋዜጥኛ አልፎም ስደተኛ ነኝ የሚለውን ጸረ ህዝብ ግለሰብ ይመለከታል ። ይህ መሰሪ ገና ወያኔን ተቃውሜ ተሰደድኩ ሲል የለም ይህ ሰው የወይኔና ከዚያም የአባት ሀገሩ የ ኤርትራ ሰላይና ቅጥረኛ ነው፤ አማራውን ሕዝብ ዲያብሎስ አድርጎ በኦሮሞዎች ሊያስጨርስ ቡርቃ ዝምታ ብሎ በጻያፉ የከተበ የወዳቂ ውዳቂ የሆን ማፈሪያ ግለሰብ ነው፤ የወያኔ እፎይታ ባለጌ መጸሔት አዘጋጅ ነበር፤ ተራራ ያንቀጠቀጥ ትውልፍ ብሎ የወያኔ ርካሽ ቅጥፈት መጽሃፍት ብሎ ያዘጋጀ ነው ብሎ ከመጀመሪያው ሲጋለጥ እነ ፕሮፌሰር ጌታቸው ሳይቀሩ አሌ ብለው ሲያዳንቁት እንደነበር የምንረሳው አይደለም። ልማድ በሽታ ነውና ይህ ከሀዲና ጸረ ኢትዮጵያ የስደተናው ማስታወሻ ብሎ ያቀረበውን ዝቃጭ ማየቱ ይበቃል ። ይህ ከሀዲ እየተጋለጠ እያለ ነጻነት አሳታሚ የሚባለው ድርጅት ሊያትምለትና ሊያሰራጭለት መነሳቱ ለትዝብት የሚዳርገው ይሆናል ።

ወያኔ የውስጡ ክፍፍልና ቅራኔ እየባሰ እንጂ እየቀነሰ አይደለም ። የሙስና እቴጌ በሆነችው በአዘብ ዙሪያ ቀንጠብ ቀንጠቡ ተጧጡፏል ። ደፍሮ የሚነካት ገና ባይመጣም ስልጣኗ በመዳከም ላይ መሆኑ ደግሞ የሚታይ ነው ። ወያኔ አማራው ኦሮሞው ሁሉም እስላሙም ክርስቲያኑም ሊነሳብኝ ነው የሚል ፍራቻ ስላየለበት ወደ አባት ሀገር ኤርትራ ጠጋ ጠጋ ማለቱን አጠናክሯል ። በፊትም ሲብል የነበር ነውና አስገራሚ አይሆንም ። ለህክምና ወደ አሜሪካ ከወንድሙም ከነልጆቹም ተጓዘ የተባለው ያመጥፎ ወያኔ አርከበ ዕቁባይም በዚያው ሳይቀር አይቀርም ተብሏል። ቀረ አልቀረ ለውጥ የሚያመጣ ባይሆንም ። በትግራይ በ አባይ ወልዱና በደብረጽዮን ተከታዮች መካከል ክፍፍልም ግጭትም ተከስቷል-- ይባባስ የምንለው ነው ። የወያኔ ኤኮኖሚ በ ıı በመቶ በዓመት እያደገ ነው ተብሎ ቢቀባጠርም ሀገር አቀፍ ድህነት ከፍተና ደረጃ ደርሷል ። ረሀብ አበቃ ቢባልም ከአፍሪካ ሶስት ለረሀብ የተጋለጡ ብሎ የተባበሩት መንግሥታት ተቋም ካጋለጣቸው ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት ። መንገድ አዳሪው ግማሽ ሚሊዮን አልፏል። በዘመናዊ ባርነት ደረጃም ኢትዮጵያ ከዋናዎቹ ወንጀለኞች ውስጥ ተመድባለች ። አርሶ አደሩ ወደ ባስ ድህነት (የሚታሰብና የሚገመት ከሆነ) እየተወረወረ ነው ።ወያኔ በሰራዊት ደረጃ እያደገ የመጣውን ቅውስ ያበረደለት መስሎት ነጋ ጠባ ለመቶ አለቅነትም ብቃት የሌላቸውን ጀኔራል እያለ ይሾማል--ዋናው መለኪያ ትግሬነትና ለወያኔ ታማኝት ነው ። በዚሁም በሽተኛው ሳሞራም ተኪ ተዘጋጅቶለታል ። ከዚሁ የቀውስ ሁኔታ ጋር በተያያዘ የወያኔ ባልስልጣኖች ወደ አውሮጳና አሜሪካ እየተጓዙ ስብሰባዎችን ማድረግ፤ የ ኑ ጥሪን ማቅረብ ቀጥለዋል-- ይህን የወያነ ጫጫታ ሰምተው ለመጪው ምርጫ ብለው መቋመጥ የጀምሩም እንዳሉ ተደርሶበታል ። ወደ አዲስ አበባና ሌሎች ቦታዎች እየበረሩ ቤት እንሰራለን ብለው የሚዳከሩ ሞኞች አሁንም አሉ--ከወያኔ ጋር የሰራና የተገነባ ሁሉ ወያኔ ሲያበቃለት የሚያልቅለት መሆኑን ዘንግተው ።ለማንኛውም በግርግሩና ቀውሱ መሀል ሙስናውም ሀገር ማድማቱን ቀጥሏል ።

ወያኔ ከከውጪ ለመውጣት ዋናው መሳሪያ የሕዝብን ጎራ መከፋፈል መሆኑ ይታወቃል ። ነገር ከተበላሸ ደግሞ ወደ ሓራሬ ሳይሆን ወደ ትግራይ ለማቅናት ደግሞ የ የፈረደበትና እሳከሁንም አልሰራ ያለው የትግራይ ትግሪኚ ዕቅድ እየተቀሰቀስቅ ነው ። በክፍፍሉ መስክ ደግሞ ሙስሊሙ ዜጋ ላይ ያተኮረ ሲሆን አሁን ደግሞ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተብየው ከስብሓት በተሰጠው መመሪያ ደግሞ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮችም ላይ ጥቃቱ ተጀምሯል ። ድርጅቶችን በተመለከተ የወያኔ ከፋፋይ ሴራ ይበልጥ ዕድል ያገኘ ይመስላል--ከፋፋዮቹ በየድርጅቱ እንዳበደ ውሻ ሊናከሱ ሲሯሯጢ ይታያሉና ። ወያኔ እየተከተለ ባለው የተሳሳተ ፖለቲካ የሀገራችንን መሬት ለባዕድ ጦር።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ምን ይሰማ……አገር?



**“ የነጻነት ዋጋ ስንት ነዉ ?”**
(በአቶ ግርማ ሰይፉ ደራሲነት በቅርቡ ለሕትመት የበቃ መጽሐፍ ርዕስ ፤ ዘሐበሻ ድረ ገጽ፤ ኦገስት ፳፱ ቀን ፪፻፲፫ እንዳስተዋወቀዉ ፤)

*** እንደገበያተኛዉ ይለያያል ። ባህር ማዶ ላለዉ ከርሳም ግን የነጻነት ዋጋ ከ40/60 መኖሪያ ቤት የማይበልጥ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ።**

//

**“ኢትዮጵያ ከሁለተኛዉ የዓለም ጦርነትበኋላ የተፈጠረች አገር ነች ።”**
(የሻቢያዉን አምባገነን ኢሳያስ አፈወርቂን ጠቅሶ ሪፖርተር ጋዜጣ መስከረም ፬ ቀን ፪፻፮ ዓም ያወጣዉ ዜና ፤)

**** ልዩነታችሁ ትንሽ ነዋ ። ወያኔዎችስ “ የመቶ ዓመት ታሪክ”ን ትለፍፉ አልነበር እንዴ ?.... አንዱ ዘራፊ ከደረመሰዉ ክምር ሌለኛዉ የሽክሙን ያህል ቢያነሳለት ጉድ አያሰኝም ። ባይሆን፤ ከጅምር አንስቶ ከታሪክና ከዘመን ቁጥር ያዛነፋችሁን ዕቡይ የኔታ እስከመቃብር ተከተሉትና ቢያንስ እምነት ነበረን በሚል ልትገደሩበት ያስችላችኋል ።***

//

**“ከኤርትራ በኩል ጠቅላላ (የምናገኘዉን ) ድጋፍ ሳይ፤ በአሁኑ ሰዓት ላይ በአራት ኮከብና በአምስት ኮከብ ሆቴሎች ዉስጥ ሆኖ የሚደረግ ትግል አድርጌ ነዉ የምመለከተዉ ። “**
(አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ ከኢሳቴ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ሴፕቴምበር ፬ ቀን ፪፻፲፫ እንዳስረዱት፤)

****ምን አለፋዎ ?/ ባይነግሩንስ ወዘናዎን በማየት ብቻ የበረሃ ኑሮ እንደደላዎት ማወቅ ይሳነናል ብለዉ ነዉ ?... ለመሆኑ ኤርትራ ዉስጥ ፍየል ስንት ገባ ?? የሆድ የሆድዎን አዉጥተዉ ቢጨዋወቱ ሰሚዉንም ይቀልለዋል።... “.ሻቢያ ለኢትዮጵያ ህልዉና የሚበጅ መፍትሔ የሚያመጣ ኃይል ቀልቦና አስታጥቆ ሊያሰማራ ነዉ ፤” ለሚለዉ ፉገራዎ ግን ጆሳጆል አድማጭ ይፈልጉለት ።***

//

**“የዓመቱ ምርጥ ባንዳ ማን ነዉ ?”**
(የኢትዮጵያ ሰማይ ጦማሪ ድረ ገጽ ፤ ሴፕቴምበር ፲ ቀን ፪፻፲፫ (በእንግሊዝኛ)

**** ምነዉ ምነዉ ፤ አገር ከሞላ ባንዳ አንድ ብቻ?/ ባይሆን ዉድድሩን በየዘርፉ አድርጉልንና ቀንዳም ቀንዳሙን በስሙ እየጠራን እንምረጥልዎ ።***

//

**“ነጻነት በገደብ”**
(መስፍን አረጋ የተባሉ ጸሐፊ መስከረም ፪፻፮ ዓ.ም በኢትዮሜድያ ድረ-ገጽ ላይ ያስነበቡት ጽሁፍ)

**** ከሠላሳ ዘጠኝ ዓመታት በኋላ አቀንቃኞቹ አቅቷቸዉ የወረወሩትን መፈክር ከየትኛዉ የቆሻሻ መጣያ ቆፍረዉ አወጡት ?...ደግሞም እኮ አወቅን አወቅን የሚሉቱ “ዲባቶዎች” (ራሳቸዉን አግዝፈዉ ለማሳዬት ሲሉ ) እያሳነሱት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመጣጥፍዎ እንደሚሉት መደዴነት የለበትም ።ሕዝብማ ክቡር ነዉ ። ባይሆን ፤ጥሬን ከብስል ሳይለዩ በአንድ ሙቀጫ ለመዉቀጥ መነሳት ነዉ መደዴ የሚያስብለዉ ፡***

//

**“ ሰማያዊ ፓርቲ ሕገ መንግሥት አረቀቀ”**
(ጎልጉል ድረ ገጽ ሴፕቴምበር ፳፰ ቀን ፪፻፲፫ የዘገበዉ ዜና )

***“ያዋከቡት ነገር ምዕራፍ አያገኝም፤” ...ነበር ያለዉ ታላቁ ድምጻዊ ?/ ከፈረሱ በፊት ጋሪዉ አልቀደመባችሁም ሰማያዊዎች ?? ...ደግሞም እኮ የአርቃቂ ኮሚሰዮን ሰያሚ ሰማያዊ ፤ የኮሚሰዮኑ አባላትም ሰማያዊ ፤.... ሁሉ ነገር ሰማያዊ በሰማያዊ ሆነና ከወያኔዎቹ የተጠጋጋ አሠራር መሰለባችሁ ።***

ገጽ 3 የዞረ

ሰፈርነት ከመስጠቱ ሌላ ወደ ሶማሊያም ጦር ልኮ በዚያ በሚያካሂደው አሜሪካን ጠቃሚ ጥቃት ለአደጋ ህዝብን አጋልጧል ። በኬንያ በዌስትጌት የተከሰተው ጥቃት ነግ በአዲስ አበባ በ............ ወዘተ ሊደርስ የሚችል ነው ። ሶስት ሶማሌዎች ቦምብ ሲያዘጋጁ ፈነዱ ወይም ተያዙ ዓይነቱ ልፈፋ ሊመጣ የሚችለውም ህዝብ እንዲዘነጋ የሚያደርግ አይደለም ። ከሶማሊያው ጦርነት የወያኔ ጀኔራሎች እያተረፉ ለመሆናቸው ደግሞ ምስክር ጥሩ አንባልም ። ኮንዶሚኒየም ወይ በርካሽ የኪራይ በት የሚለውም ማታለያ ያለውን የቤት እጥረት ሆነ የከተማይቷ ይዘት ሁሉ መበለሻሸት የሚሸር አልሆነም ። ውሃና መብራት በፈረቃ መሆኑ አልተወገደም ። በለስ፤ግልገል ግቤ 1 ና 2 በቂ መብራት ሀይል ለሃገር አቅርበው ለሽያጭም ይተርፋሉ የተባለውን ሜጋ ዋት ሀይል እንኳን ማምረት ገና አልቻሉም ። መስመር ለመዘርጋት ኮንትራቱን የወሰዱት የቻይና ኩባንያዎች-- በጉቦ ያገኙት ዕድል ነው-- ስራቸውን አላጠናቀቁም ። ይህ በዚህ እንዳለ ለተሀድሶ ግድብ ተብዬው ቦንድ የገዙና ገንዘብም የለገሱት --ወያኔዎቹ ሳይሆኑ የዋሆቹ--ላም አለኝ በሰማይን ታቅፈው ቀጥለዋል ። ግብጽ የራሷ ችግር ወጠራት እንጂ ዕድሜ ለወያኔ በኢትዮጵያ ላይ አደጋ ልትሆን በቻለችም ነበር ። አይነቁ የዋሆች ግድቡን (20 በመቶው ስራ ተጠናቋል ሲል ወያኔ ዋሽቷል!) እንንነብኝ ሲሉም በርከትከት ብላችሁ ይቻል ይሆናል በሚል በመሸንት ላይ ነው ።

የሕዝብ መነሳሳት ካለፈው በተሻለ ሁኔታ እየታየ ነው ። የወያኔ ቀውስም እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አይደለም ። የጎደለው ትግሉን ሊመሩ የሚችሉት በተጨባጭ ትግል ሊሰማሩ እስካሁን አለመቻላቸው ብቻ ነው ። ይህን ድክመት እንዴት ማስወገድ ይቻላል በሚለው ላይ ሚዛን ያላቸው ድርጅቶችና ሀገር ወዳድ ግለሰቦች ሁሉ ማተኮር አለባቸው ። ሌላው ሁሉ ትርፍ ነው ። ይህን በተመለከተ ደግሞ በሕዝብ ጎራ ያሉ መስለው ትግሉን የሚጎዱትን ማስወገድ ተገቢ ነው ። የሻዕቢያው ሰላይ ጋዜጠኛ አንድ ምሳሌ ነው ። ምሁር ተብሎ አማራን ፍጁ እንረድ ጥሪን ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ያስተጋባው ሌላ ምሳሌ ነው ። ድርጅቶችን ለመከፋፋልና ለማውደም በተጨባጭ እየጣሩ ያሉትም የሚጠቀሱ ናቸው ። ነቃ እንበል፤ ሰፈራችንን እናጽዳ፤ እንደራጅ እንሰባሰብ ።

**ከዚህ ባሻገር ግን እስቲ ቀጣይ ጥቆማዎችን ልብ እንበላቸው----**

* በላምፓዱሳ (ጣሊያን) ወደብ መርከብ ሰጥሞ ከ350 በላይ ኤርትራውያን ማለቃቸውን ምክንያት በማድረግ ዓለም በኤርትራ ሁኔታ ላይ ማተኮር ጀምረዋል ። በነገራችን ላይ በዚህ ወደብ ሆን በየመን ወደብና ብቦሳሶ ወዘተ ስድተኞች ሲያልቁ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም አይደለም ። በሊቢያ ስደተኞች የሚደርስባቸው ሰቆቃም ከዚህ በፊት የተዘገበ ነው ። በ ኤርትራ ያለው የፖለቲካ ኤኮኖሚያው ሁኔታ አስከፊና አሳሳቢ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ኢሳያስ አፈወርቂም በአምባገነናዊነት መቀጠሉን ታዛቢዎችና የአገዛዙ ተቃዋሚዎች በትኩረት እየተቹ ናቸው ። ሁኔታውን በቅርብ ተከታተልን የሚሉ ክፍሎች ደግሞ የኢሳያስ የስልጣን ዕድሜ ማብቂያው ደርሷል ሲሉ የተኪዎች ጥያቄ ግን አሁንም አሜሪካንን አሳሳቢ ሆኖ ይገኛል ብለዋል።

* በጉራ ፈርዳና ሌሎች ቦታዎችም ጸረ አማራው ዘመቻ መቀጠሉንና በርካታ የመኢአድ አባላትም እየታሰሩ መሆናቸውን ዘናዎች ደርሰዋል ።

* በዴንቨር (አሜሪካ) ስሙን ቀይሮ ይኖር የነበረውን አረመኔ የቀይ ሽብር ወንጀለኛ አንድ ቆራጥ ዜጋ አጋልጦ ካስያዘው በኋላ ሌሎች መሰል ወንጀለኞችንም በይፋ ማጋለጡና ወደ ፍርድ ማቅረቡ የሚቀጥል መሆኑ ተነግሯል ። ስም ዝርዝሮችም ተሰብስበዋል የሚልም መረጃ አለ ።

* ጸረ ሕዝቡ ስብሓት ነጋ ላይ የተወሰኑ ቆራጥ ዜጎች በአሜሪካ ቢሰለፉበትም ይህ ዘረኛ ግለሰብና ግብረ አበሩ በአንድ ዜጋ ባደረሱት ድብደባ እንኳን ተናዶ በርካታው ኢትዮጵያዊ ተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ አለመቻሉ የሚያስተዛዝብና አሳዛኝም ነው ብለዋል ።

* ከተመሰረተና አያሌ ጥቃቶችን ተቋቁሞ ትግሉን ከቀጠለ 41 ዓመት በሆነው ኢሕአፓ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻውም አሁንም በሀገር ቤትና በውጭ ሀገር በወያኔና በወንጀለኞች አቀነባባሪነት በመካሄድ ላይ ነው። ወያኔ ከዚህ በፊት ባወጣው የ 52 ገጽ መመሪያ ውስጥ በተወሰኑ የአመራር አባላት ላይ ማተኮርና ማጥቃት ባለው መሰረት በድርጅቱ የተወሰኑ አመራር አባላት ላይ ዘመቻው በርብርቦሽ መልክ መካሄዱና በዚህም ዘመቻ ቀደም በአፍራሽነት ተሰማርተው ውድቀት ያጋጠማቸውም ከየጉዳዳቸው ወጥተው እየተሳተፉ መሆናቸው ተጠቁሟል ።

- ሀይለማርያም ደሳለኝ ከዓለም አንደኛ እየሆነበት የመጣው ክስተት እንደእሱ አማካሪ፤ ምክትልና ረዳት ያለው ጠቅላይ ሚኒስቴር ባለመኖሩ ነው የሚል ትችት በመደመጥ ላይ ነው። ሌሎች ደግሞ--ምኞት ገና አልታገደምና-- ሀይለማርያም በእውን ጠቅላይ ሚኒስቴር ነው ብለው እሱም የማያምነውን ያምናሉ ።

ከገጽ 1 የዞረ

.... 70 ጀኔራል ተብየዎች ተሾሙ

6 ብርጋዲየር ጀኔራል ተብየዎች የሜ/ጀ/ልነት.... 1 ሜ/ጀ/ል ተብየው የወያኔን የሌ/ጀ/ል ማዕረግን አግኝተዋል፡፡

የወያኔው ሜ/ጀ/ል ተበየው ዮሐንስ ገብረመስቀል ከሳሞራ የኑስ ጋር ግጭት በፈጠረውና ከዳርፉር ከሔደበት የሰላም ማስከበር ተጠርቶ በጡረታ እንዲሰናበት በተደረገው ሌ/ጀ/ል ታደሰ ወረደ ምትክ የተሾመ ሲሆን ይህም ርምጃ የሳሞራ የኑስን የበላይነት በግልጽ ያሳያል በማለት ታዛቢዎች አስተያየት ይሰጣሉ፡፡

በወያኔው ሌ/ጀ/ል ተብየው ሣዓረ መኮንንና በ ሳሞራ የኑስ መሀከል ተፈጥሮ የነበረው የእርስ በርስ ሽኩቻና የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ወደ ሌሎቹ ጀኔራል መኮንኖች ጭምር ዘልቆ ሲያተራምሳቸው በሚል በጠራው ስብሰባ ላይ እነ ሳዓረ አንገታቸውን ደፍተው እንዲወጡ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል


ከኢሕኣፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

ስልክ፡ (202) 291-4217
ኢሜል፡ espic@aol.com
ፖስታ፡ EPRP
P.O. Box 73337
Washington, DC. 20056
ድረ ገጽ፡ eprp.com

ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ Finote.org




ከኢሕኣፓ ወክንድ (EPRPYL) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም የቻላል

ስልክ፡ (202) 291-5832
ኢሜል፡ eprpylnew@gmail.com
ፖስታ፡ EPRPYL
5309 Georgia ave.
Washington, DC. 20011
ድረ ገጽ፡ eprpyl.com

## የቦረና ነጌሌዎቹ የኢሕኣፓ ወጣቶች ሕዝባዊ ገድል በጨረፍታ ቅኝት (ምንጭ መጽሀፍ፤ "ያልታደለ ትዉልድ" ኣዉነትኛ ታሪክ) (ደራሲ፤ ኣብዲ ኣብዱላሂ)

# የመምህር ወርቅዓለማሁ ንጋቱ መራር ትዝታ



መምህር ወርቅአለማሁ ንጋቱ (መራር ትዝታ)

በምሬት ተወዳዳሪ ያልነበረዉን ሕይወት በመግፋት ላይ በነበርንበት በዚያንየጽልመት ዘመን በሮችና መስኮቶች በላያችን ተከረቻችመዉ ተዘግተዉብናል።እንዲያም ሆኖ ግን እንቅስቃሲያችን አላቆመም ።በተጣበበ ሁኔታም ቢሆን የፓርቲጋዜጦችን እናነባለን ፤ መረጃዎችን እንለዋወጣለን ። እነማንእንደታሰሩ፤ እነማን እንደተረሸኑ፤ እነማንስ አገር ጥለዉ እንደኮበለሉእንሰማለን።ተስፋ የሚያስቆርጥ ጊዜ ነበር ፤ ድርጅታዊ ሥራዉ ግንቀጥሏል ። በድርጅቱ መጠለያ ቤት የነበሩትም እነፈቃዱ ሙላትን የመሰሉ ጓዶች፤ በፋሺስቶች እጅ ተዘልዝሎ ከመሞት እየሮጡ ማምለጥን መርጠዉ በጥይት ተደብድበዉ መሰዋታቸዉ ተነገረን። ከዕለት ወደዕለት የሞት ኮቴ ከበስትኋላችን ይበልጥ ሲቀርበን ይሰማናል ። የየልቦናችን ቅኝት ግን፤ ዛሬም ሳይለወጥ "ድል ለሰፊዉ ሕዝብ / ...ድል ለኢሕአፓ/"ን ያስተጋባል ።

የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም ማለዳ ላይ በመስኮት ቀዳዳ አጮልቄ ደጁን ሳማትር ፖሊሶችንና የደኅንነት ታጣቂዎችን እየመራ የመጣ አንድ ሰዉ የመኖሪያ ቤታችንን ሲጠቁም ተመለከትኩ። ሁኔታዉን ለወንድሜ ለሙሉዓለም ንጋቱ አሳይቼው እንድንሸሽ አሳሰብኩት ። ፈቃደኛ አልሆነም ። እኔ ግን የበስተጓሮዉን አጥር ዘልዬ በመዉጣት ወደ ት/ቤት አመራሁ ። እናም ቤት ዉስጥ የነበሩትን ድርጅታዊ ንክኪ የነበራቸዉን ቁሶች ከነሚገኙበት ሥፍራ ዘርዝሬ ለታናሽ እህቴ በማስረዳት እንድትሰዉራቸዉ ነገርኳት ።

በመመለስ ላይ ሳለሁ ሳላስበዉ ከፊቴ ሽጉጥ ተደግኖብኝ እንድቆም ታዘዝኩ ። አላደረግኩትም ፤ ሩጫ ጀመርኩ ። እየተኮሱ ያሳድዱኝ ጀመር ።ከአጥር ወደ አጥር እየዘለልኩ ሁለት ቀበሌዎችን አካለልኩኝ ።በመጨረሻዉ በመዳከሜ ዙሪያዬን ተከብቤ ተያዝኩ ። እጆቼ የኋሊት ተጠምዝዘዉ አፈሙዞች ተደግነዉብኝ በአጀብ አዉራጃዉ ፖሊስ ወደሚገኘዉ የምርመራ ማዕከል ተወሰድኩ ።ወደ ማሰቃያዉ ክፍልም ገፈታትረዉ አስገቡኝ ። እጅጉን ከሚጠነባዉ ከዚያ ክፍል ዉስጥ ከነበረዉ ብርሃን ጋር ዐይኖቼ ገና ሳይላመዱ በቡጢ ፤ በዱላና በጉማሬ አለንጋ ተረባረቡብኝ ። በዱላዉ ዉርጅብኝ ራሴን ስቼ ወደቅኩ ። ከደቂቃዎች በኋላ ባንኜ ነቃሁ ። ጸጉሬን ጨምድደዉ ካቀኑኝ በኋላ ዉሃ እያፈሰሱብኝ እንደነበር አየሁ ። ገራፊዎቼ ከብበዉኛል ። ዳዊት ያዕቆብ ነበር ዉሃ የሚያፈስብኝ ። ታደሰ ቦጋለ የሚባለዉ ደግሞ "... ልጄ ፤ አይዞህ የአብዮቱ ጠበል ነዉ ። ቀና በል እና ጠጣ /" ይለኛል ። ወለሉ ላይ ዘርፈጥ አልኩ። በጫማ ጥፊ የተመታዉ ብልቴ ህመሙ ቀስፎ ይዞኛል ።....በአፌ ደም ይፈሳል ።....ሻለቃ ከፍያለዉ ፤ "ትፋ /" ይለኛል ። እተፋለሁ ። ደሙ ግን አይቆምም ። " ሽጉጡንና ቦምቡን የት ነዉ የደበቅከዉ??......ከእኛ ዉስጥስ ማንን ልትገድሉ ነበር ??? .....በድርጅቱ ዉስጥ ያለህ የሥራ ድርሻ ምንድነዉ ???" በጥያቄ አጣደፉኝ ።

ለማንኛቸዉ መልስ ይሰጣል ?? የሞት ሞቴን "እረ ምንም አላዉቅም ፤" አልኳቸዉ ።....በሳቅ ክፍሉን ሞሉት ። አቶ ታደሰ በከባድ ጥፊ ወለሉ ላይ ጣለኝ ። ጆሮዬ ተደፈነ ። አፋቸዉ ሲላወስና የፊታቸዉ ገጽ በቁጣ ሲነድ ይታየኛል እንጂ የሚሉት አይሰማኝም ። ቀድሞዉኑ ከእጃቸዉ ላለመግባት ባደረግሁት ሩጫ ደክሜ ነበርና ተዝለፍልፌ ተዘረጋሁ ። ራሴን መሳቴ ከግልግል የሚቆጠር ነዉ ። ወዲያዉኑ ግን ዉሃ አፍስሰዉ ከቀሰቀሱኝ በኋላ ልብሴን አስወልቀዉ በዉስጥ ሱሪ ብቻ ወንበር ላይ አስቀመጡኝ ።

# ትላንትና

የፖሊስ አዛዡ ሻለቃ ከፍያለዉ አድገህ ፤ " ገለል በሉልኝ ፤ ደም እንዳያበላሻችሁ / ገላግለዉ ...አታወጣም ?/" በማለት ተሸከርካሪዉን ባለ ነጥብ 38 ሽጉጡን ጥይት እያጎረሰ ያንቀጫቅጫል ። እነዘርዓይ ደግሞ "ቆይ ቆይ አትግደለዉ ....ይናገራል፤" በሚል ይከላከሉታል ።ቁጥራቸዉ ከአስር በላይ ሲሆን ሁለ ነገራቸዉ ሕጻን የሚያስፈራሩ ያስመስልባቸዋል ። በመቀጠል ሻለቃዉ "ዘወር በሉልኝ /"ብሎ በመደንፋት ገለል ካስደረጋቸዉ በኋላ ወደ እኔ ተረማመደና " አፍህን ክፈት /"ብሎ አዘዘኝ ። እንዳለዉ አደረግኩለት ። የሽጉጡን አፈሙዝ አፌ ዉስጥ ከተተና " አትናገርም??" አለኝ ። ገና ለመናገር ከንፈሮቼን ማንቀሳቀስ እንደጀመርኩ ጥርሶቼ የረገፉ እስኪመስለኝ ድረስ የሽጉጡን አፈሙዝ አፌ ዉስጥ ከትቶ አማሰለብኝ ። ቀጥለዉ እጆቼን የኋሊት ጠፍረዉ አሰሩኝ ። በአቀማመጤ ከተጋለጡት ጭኖቼ ላይ በጉማሬ አለንጋዉ እጀታ ክፉኛ ደበደቡኝ ። በዚሁእንዳይበቃኝ፤ ወታደር ሰለሞን እየተንጠራራ የእግሮቼን ጣቶች ይረግጠኝ ነበርና ሕመሙ እስከ ጭንቅላቴ ይነዝረኝ ነበር ።ከሥቃዬ የተነሳ በምሬትጮህኩኝ። ሞቴንም ተመኘሁ ።የተዋሃደኝን "የኢሕአፓ ዲሲፕሊን" ለመስበር ያቀዱት ከፍያለዉ ፤ ዳዊትና ዘርዐይ የተባሉት ገራፊዎች "ወፌ ይላላዉ" እንዲቀጥል አዘዙ ።ተሰቀልኩ ። በጠረጴዛና ጠረጴዛ መሀከል በተዘረጋ እንጨት ላይ አንጠለጠሉኝ ። አሮጌ ካልሲ በአፌ ከጠቀጠቁብኝ በኋላ መናገር ስፈልግ ጣቴን እንዳንቀሳቅስ ተነገረኝ ። እየተፈራረቁ ወረዱብኝ ። እሳት የፈሰሰበት ሰዉነቴ በሥቃይ ብዛት ደከመ ። በጣቴ ምልክት ከሰጠኋቸዉበኋላካልሲዉን ከአፌ አዉጥተዉ ከተሰቀልኩበት አወረዱኝ ። በረዢሙ ተነፈስኩ ።" በል ተናገራ / ...ተናገር/" አሉኝ ።

መናገር አቃተኝ ። አፌ ብቻ ሳይሆን ዉስጤም ደርቋል ።.....ምራቅ የለም ። ከንፈሮቼ በዕብጠት ተነርተዋል ። እንደምንም "ዉሃ" የምትለዉን ቃል በምልክት ገለጽኩላቸዉ ። አገጬን ይዘዉ ፊቴን ካንጋጠጡት በኋላ ዉሃ ከለበሱብኝ ። ትንታዬን ተከትሎ ቋቅ አለኝ ። ደም የተቀየጠበት የአክታዬ ልጋግ ለራሴዉም አስጠላኝ ። ወዲያዉ በእርግጫና በጉማሬ አለንጋ አጣደፉኝና "ለማታ ተዘጋጅ ፤ የሠራኸዉን ዘርዝረን ሳናነብልህ በፊት ካልተናገርክ ወላጆችህ ፊት ወስደን እንደፋሀለን ፤" በማለት ዳዊት ማስፈራሪያዉን (እዚህ ላይ በማንጠቅሰዉ ) አስጸያፊ የኦሮሚኛ ስድብ ደመደመዉ ።

ከምርመራዉ ክፍል ወጥቼ ወደ መታጎሪያችን ለመሄድ ተሳነኝ ። ዳህኩኝ ፤ዳዴም አልኩ ። አልሆነልኝም ። በግድ አስነስተዉኝ "ርገጥ" እያሉ አስገደዱኝ ። በእግሮቼ ለመርገጥም ሆነ ለመቆም ግን አልቻልኩም ። ፖሊሶች በድጋፍ ይዘዉ ሲወስዱኝ ፤ ጠዋት ላይ አብሬዉ ቁርስ የበላሁት አባቴ በድንጋጤ ደርቆ ሲያዩኝ ዐይን ለዐይን ተጋጨን ። ዐይኖቹ በዕንባ ተሞልተዉ ፊቱን አዙሮ ሄደ ።ለአባቴ አዘንኩለት። ፖሊሶቹ ከመታጎሪያችን ክፍል አስገብተዉ እንደወረወሩኝ በሆዴ ተደፍቼ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩኝ ፤ -በቁርጡ ሞት የተሻለ ነዉ ። ጓዶች ሰዉነቴን በቅባት እያሹ አጽናኑኝ ። አበረታቱኝም ። ከእኔ ቀደም ብለዉ የተያዙ እንደመሆናቸዉ ስለዉጪዉ አስከፊ ሁኔታ ጠየቁኝ ። በዝርዝር መለስኩላቸዉ ፤ በሰቀቀን ተኮራምተዉ አዳመጡኝ ። በዚያች ቅጽበት የሁላችንም ጭንቀት የድርጅታችንን የኢሕአፓን ዕጣ ፈንታ የሚመለከት ነበር ።

ቀዳሚዎቹ ታሳሪዎች ማታ ለሚጠብቀኝ ምርመራ ህሊናዬን ለማዘጋጀት የየበኩላቸዉን ታክቲኮች ያዋጡ ጀመር ። ሊደበቁ የማይችሉና አስቀድመዉ ለጠላት የተጋለጡ ድርጅታዊ ምስጢሮችን በመካድ እስረኛዉ ብዙ እንዳይሰቃይ ለማድረግ በአራቱም የእስር ክፍሎች የነበሩ እስረኞች ግድግዳ ተሰርስሮ በተዘጋጁ ስዉር ቀዳዳዎች አማካይነት የመረጃ ልዉዉጥ ያደርጋሉ ። የተፈጥሮ ህግ ነዉና ቀኑ ደነጋገዘ ። በቀኑ ምርመራ የተጎዳዉ ሰዉነቴ ሕመሙ እየቆዬ ይበልጥ እየተሰማኝ መገላበጥ ተስኖኛል ። እንደቀኑ ከተደበደብኩ ሰዉነቴ ላይ በተለያዩ ቦታዎች የተቋጠረዉ ጥቁር ደም መፈራረጡ መሆኑ አሰጋኝ ። በልቤ ጸለይኩ ። ያለመምሸቱንም ተመኘሁ ።ሆኖም ማታ ላይ የገራፊዎቹ ላንድሮቨር መኪና ወደ እስር ቤቱ ግቢ ዘለቀች ። እስረኛዉ በሙሉ ከየተንጋለለበት እየተነሳ ተቀመጠ ። ገራፊዎቹ ተሳክረዋል ። " ዘብ/ ዉሾቹ አሉ ?" በማለት በተለፋደደ ምጸት ከጠየቁ በኋላ የእስር ክፍላችንን በር አስከፍተዉ ንጉሤን ጠርተዉ ወሰዱት ። አቆይተዉ መለሱት። ክፉኛ ተደብድቧል ። በዚያ ምሽት ሌላ ተመርማሪ አልጨመሩም ። ቢሆንም ከአሁን አሁን ይመጡ ይሆናል በማለት በጭንቀትና በሕምም ስሰቃይ እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም ። ንጋት ላይ በቅዠት የተሞላ እንቅልፍ አሸለበኝ ።

በማግሥቱ ረፋዱ ላይ ተጠራሁ ። የግዴን ተነስቼ ለባበስኩ ። በዚያች ክፍል ከታሰርነዉ ሁሉ በዕድሜ ትንሹ እኔ ነበርኩና አዉግቸዉ እርገጤና ሌሎቹ ጓዶች " አይዞሽ አትፍሪ፤" በሚል የታላቅ ማበረታቻ ሸኝተዉኝ ወጣሁ ። በስተ ምሥራቅ በኩል በየቀኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ መሰሎቼ ስቃይ የሚቀበሉበት የምርመራ ክፍል ከመሰብሰቢያ አዳራሹ ጎን ተገሽሮ ይጠብቀኛል ። የታሪክ ምጸት ሆነና ያ ቤት ከአርባ ዓመታት በፊትም አርበኞቹ አያቶቻችን በፋሺስቶች እጅ ወድቀዉ የተገረፉ የተሰቃዩበት ሥፍራ ነበር። በኢጣልያ ወረራ ወቅት በእስረኞች ጉልበት የተሠራ ሲሆን በኛዉ ጊዜም የእስረኞች ጉልበትና ጽናት ይፈተንበታል። ልዩነቱ የአሰቃዮቹ ዘርና የቆዳ ቀለም ብቻ ነበር ። "ቦምቡን ዬት አደረግከዉ ?/.... ሽጉጡንስ ?/" አንባረቁብኝ።

ልባቸዉን ሊያራራልኝ ይችላል ብዬ በገመትኩት መጠን ድምጼን አለስልሼና ተቅለስልሼ ፤ "እባካችሁ ፤ስለዚህ ጉዳይ የማዉቀዉ ነገር የለም፤" አልኩ። ዱላዉ ቀጠለ ። ልብሴን አስወልቀዉ ወለሉ ላይ አስተኙኝ ።ከዚያም እጆቼንና እግሮቼን ለአራት ወጥረዉ በመያዝ በጉማሬ አለንጋዉ እጀታ እየተንጠራሩ መቀመጫዬንና ጀርባዬን በፈረቃ ደበደቡኝ ። በስቃይ ብዛት በጣም እጮህ ነበር። እነርሱም በበኩላቸዉ በጩኸት "ተናገር /...አዉጣ/... አንተ ግልገል ፋሺስት እመን/" ይሉኛል ።
"እናገራለሁ /" አልኩ ።... ዱላዉ በአንድ አፍታ ቆመ ። "በል ከመጀመሪያዉ ጀምረህ ....እንዴት እንደገባህ ፤ ምን እንደሠራህ አዉጣ /....ብትደብቀንና ሌላ ሰዉ ቢያጋልጥህ ራስህ ላይ እባብ እንደጠመጠምክ እንድታዉቀዉ /....ደምህን ነዉ የምንጠጣዉ ፤" አሉኝ ።ገራፊዎቼን ልብ ብዬ አስተዋልኳቸዉ ። በተለይ ዳዊትና ዘርዐይ እዉነትም ደም የጠማቸዉ አጋንንት መስለዉ ታዩኝ ።

ወደ ገጽ 7ዞ ሮል

# ነጻ ሀሳብ

## <u>የማይፈርስ ምሽግ የማይወድቅ ጨቋኝ አገዛዝ የለም !</u>

የፖለቲካ ንቃትና ግንዛቤ በደከመበት ብዙሃን በስልጣን ተቀምጦ ማን ሊነካኝ የሚለውን ግብዝ አገዛዝ እውነትም ሁሉን አሸናፊ ይመስላቸዋል ። ጡንቻውን በግድያና አፈና እያሳያቸው እውነትም ማን ሊበግረው በማለት ተስፋ ይቆርጣሉ፡፤ በዚህ ላይ ደግሞ ታጋይ ነን ባዮቹ ማበር ሲያቅታቸው፤ እርስ በርስ ሲናከሱና ሲከፋፈሉ ቀቢጸ ተስፋ አለና ብትል የምንደነቅ መሆን የለብንም ። ዋናው ችግር ወያኔ ይወድቃል ሁሉም ምሽጎቹ ይፈርሳሉ በሚለው ሀቅ ላይ ሙሉ እምነት አለመኖሩ ነው ።

ወያኔ ወደ ውድቀቱ እየሮጠ ነው የሚለውን ሀቅ የማያምኑት ብዙዎች ናቸው ። አይፈረድባቸውም--ወደቀ ሲባል ዓመታት አልፈዋልና ። ነገር ግን የአገዛዝ መውደቅ ቅርበት ምልክቶች ብዙ ናቸው ። በዘመነ ሀይለስላሴ ኢሕአፓ ሲመሰረት ሕዝብ ንጉሱን ያመልካል፤ ይፈራል ይወዳልምና አትድከሙ ያሉ ጥቂቶች አልነበሩም። ግን የህዝብና የሀገሪቷን ተጨባጭ ሁኔታ የተገነዘቡት የሀገሪቷ ዜጎችና ታጋዮች አገዛዙ ወዳቂ ነው ብለው ባደረጉት የመደራጀት ትግልና የመታገል ጥረት ስርዓቱ በሕዝባዊው የየካቲት 66 አብዮት ሊንኮታኮት ችሏል ። ግልግል ። በዚህ አብዮትም ሴቱ ወንዱ፤ ወጣት ሽማግሌው፤ እስላም ክርስቲያኑ አማኙ ሁሉ በጋራ መሰለፉ ለቀጣይና ለነገ ትግሎች ሁሉ አርአያ ሆኖ ይገኛል ። ያን የአብዮት ወቅትና የዚያን ትውልድ ወኔና ጀብድ መድገሙ አቃተንና ዛሬ የተመረጠ የሚመስለው መንገድ ትውልዱን ማውገዝ፤ ማኮቸልቸልና የፈሰሰውን ደም ማራከስ ሆኖ ህሊናችንን ያጠቃል ። ዛሬ ጥራዝ ነጠቁ ሁሉ ይቻላል የሚለው መፈክር ያነ ይቻላል ማለት ድፍረትና ህይወትን ሊያስጠቃ የሚችል በነበረበት በዚያ ትውልድ ይተለፍፈና መስዋእትነትም የተከፈለበት ነበር ፡፡ ባዶ ቃል አልነበረም። መሮጥ ይቻላል፤ ከጨቋኝ ጫማ ስር ወድቆ መኖር መጠቀም ይቻላል ማለትም አልነበረም።

የወያኔ መውደቅ ታሪካዊ ህግ ነው። ወደዱም ጠሉም፤ ተፈራገጡም ገደሉም ቀናቸው መጥቷልና ይወድቃሉ። ማንም አያድናቸውም-- ተንኮል፤ ሴራ፤ ብልጠትና አፈናም መጨረሻቸውን አይለውጠውም። ይህ ውድቀት ግን በተወሰነም ደረጃ ቢሆን አላስፈላጊ ደም መፋሰስም እንዳይከሰት ከወዲሁ መጠንቀቅ ማስፈለጉ ደግሞ ግልጽ ነው ። ቅራኔዎች ተካረዋልና ። የክልል አንድ ተወላጆች በጥቅሉ የወያኔ አጃቢና ተጠቃሚ ናቸው የሚለው ድምዳሜ የተስፋፋ ነውና። የወያኔ አገዝዝ ሌሎችን እየመነጠረና ከቀዬአቸው ሁሉ እያፈናቀለ ነውና፤ ከጎንደርና ወሎ የሰረቀውን መሬት የትግራይ ብሎ ለራሱ እየበዘበዘ ነውና የቀሪው ህዝብ ምሬት፤ቁጭትና ንደትና በቀል ፍለጋ በቀላል የሚታይ አይደለም። አማራው የባሰ ጠላታቸው ነው። ሀገራቸው ሌላ ነው ። ተለጣፊ ይፈልጋሉ እንጂ ሌላ ዕይታ ወይም ግምት የላቸውም ።

ሞኞች ሀይለማርያም ተብዬው እውነትም ባለስልጣን ጠቅላይ ሚኒስቴር የሆነ መስሏቸው ይሞኛሉ። የነስብሓትና በረከት መኾዣ መሆኑንም ይዘነጋሉ ። ዛሬም ሆነ ካልጣልናቸው ነገም ስልጣን በወያኔ እጅ ነው ። ሌላው ሁሉ አጃቢ፤ተለጣፊና አልፎም ቅጥረኛ ነው፡፡ ይህ 22 ዓመት ያለፈውና በጣም የከበደን የመረረን ሀቅ ነው ። መጠታት የነበረብን ያለብን እሬት። ገና ያላሸረን መድሀኒት ምክንያቱም ተጨባጭ ሁኔታውን በሚገባ ተረድተን መደረግ ያለበትን መፈጸም ገና አልቻልምና ። ይህን ድክመታችንን በተመለከተ ደግመን ደጋግምን ብዙ ብለናልና አሁንም በጉንጭ አልፋ ስምሪት መግባቱ የሚጠቅመን አይሆንም ። ወያኔ ይወድቃል ብሎ ማመንና ይህንንም እውን ለማድረግ የሚፈለገውን መስዋዕትነትም ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለብን ማለት ነው ዋናው ቁም ነገሩ። የማይፈርስ ምሽግ የለም-- ሊያፈርሰ የተነሳ/የተነሱ ቆራጦች ካሉ ። ለጠላት ቅንጣትም ምህረት አይኖርም የሚሉ ካሉ ። ይህ አልሆን ብሎ ግን ከወያኔ መንጋ ጋር ለመደራደር ሽብ ረቡ ካየለ፤ የዘረኛውን ወያኔ ገዢነት ተቀብለን እንበርከክ የሚሉ ከበዙ፤ ለኮንዶሚኒየም ቤትና ለመሬት ምሪት (ያውም ከዜጎች የተቀማ መሬት!) ሩጫው ከበዛ፤ ሆድ ሀገርን ከቀደመ ሀገራችን ኢትዮጵያ ህልውናዋ ለከፋ አደጋ ይጋለጣል ። ሁሉም ዜጋ የሚያውቀው ሀቅ ደግሞ በወሳኝ ወቅት ዜጎች ሽብረክ እያሉ ሀገርን ጎድተው ጠላትን ጠቅመው ያደረሱት ጉዳት ከባድ መሆኑን ነው ። የጣሊያን ጊዜ ባንዶችና ዘመናዊ ባንዶች፤ በታኞችና ከፋፋዮች የሚጠቀሱ ናቸው ። ባልኖሩ ደስ ባለን ግን እንደ ተምችና አንበጣ ሲፈሉ ደግሞ ልስናስወግዳቸው መታግል የግድ እየሆነ ጊዜም ጉልበትም ጠያቂ ሆነብናል ።

በዚህ በዚያ ፍልቅልቅ እያለ ያለው የሕዝብ ትግል ገና አይሎ ድልን ሊነጥቅ አልደረሰም ። መለዮ ለባሹ ለውጥ ያመጣል ሲሉን የነበሩ ዓይነቶች ዛሬ ደግሞ ዘረኛው የወያኔ ስርአት የይስሙላ ጠቅላይ ሚኒስቴርን ይዞ ለውጥ ሊያመጣ ነው ብለው ይለፍፋሉ። ሰሚ አላጡምና ተስፋቸው ብዙ ነው ። የክፍፍል ተልኮአቸውም ደካማ አይደለምና ብዙ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን አጥቅተውና አስጠቅተው ክፍፍልን አስፍነዋል ። ግባቸው በፈለጉት እረጃም ባይሆን እየተሳካ ነውና በጋዘጦቻቸውና ስብሰባዎችም ሳይቀር እየፈነደቁ ናቸው።

የ አጭር ጊዜ ራስ ማታለያ ፍንዳቃ ነው ይብላን ለነሱ ቅጥረኞቻቸው እየተጋለጡ ናቸው፤ በታኞቻቸው ተልዕኮአቸው ታውቆ እየከሸፉ ናቸው ። ውስጣዊ ቅራኔያቸውም እየሰፋ እንጂ እየጠበበ አይደለም ። ሆኖም ግን ስንቱን ዜጋ የጨረሰው ወያኔ፤ ሀገራችንን የሸነሸነው ወያኔ፤ በብሄረ ስብ ጥላቻ ስንቱን የገደለውና ያፈናቀለው ወያኔ፤ ጎንደር ወሎን የትግራይ መሬት ብሎ የዘረፈው ወያኔ፤ ለም መሬታችንን ለሱዳን የሰጠው ወያኔ፤ ለም መሬታችንን ለቻይና፤ ህንድና አረቦች የቸበቸበውና አርሶ አደሮችን ያፈናቀለው ወያኔ፤ ስንቱን የፖለቲካ እስረኞች ደብዛ ያጠፋ የደደቢት ውላጅ፤የነፕሮፌሰር ኣስራት፤ አስፋ ማሩ፤ ተስፋዬና ሌሎችም ገዳይ ወያኔ፤ የኦጋዴን፤ ጋምቤላና ሌላውንም ሕዝብ ጨፍጫፊ ቡድን፤ ስንቱን ጋዜጠኛ ተቃዋሚ ለቃሊቲና ዝዋይ ያበቃ አፋኝ አገዛዝ፤ መሰረታዊና የእምነት መብታችን ተጣሰ ያሉትን ያሳደደና ያጠቃ ቡድን ማለትም ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው አገዛዝ በምንም ተዓምር ከቶምና መቼም የሚለውጥ ኣይደለምና ከእዚህ ዘረኛ ጥርቅም ጋር መቻቻልን፤ መታረቅን ማቀንቀን በተጨባጭ ኢትዮጵያን ማጋለጥና መካድ ነው ። ይህ ለሁሉም ዜጋ ግልጽ ሊሆን ይገባል ። ቢከብድም መቀበል የሚገባን ሀገር አድን ሀቅ ነው ።

የሀቅ ቋት ሆኖ የባጀው የኢሕአፓ ልሳን “ዴሞክራሲያ” ድሮ ድሮ ሲጽፍ የሚከተለውን ብሎ ነበር፡

“ የዴሞክራሲ ለዛ የሚታወቀው፤ቃናው የሚጣፍተው፤ በስማ በለው ሳይሆን፤ በቀጥታ ከሕዝብ አንደበት ሲወጣ፤ ከእስትንፋሱ ጋር ሲዋሀድ ነው።......በአፈሙዝ ሀይል ያገር አንድነት፤ በመዋቅር ስፋት የ ኤኮኖሚ እድገት፤ በዲስኩር ብዛት የፖለቲካ ንቃት አመጣለሁ ብሎ በሚጓዝበት አብዮታዊ ሳይሆን ዕቡይ ሂደት፤ ከድቀት ወደ ድቀት እርምጃውን እያፋጠነ ይውተረተራል ። ያገር አንድነት የሕዝባችንን ደሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት ከማክበር ይሰርጻል።ከዚህ ውጪ ዘለቄታዊ መፍትሔ ሊገኝለት አይችልም።

ብለን ነበር ዋጋ የለውም ሰሚ ባልነበረበትና አሁንም በሌለበት-- ግን ሀቁ መነገሩ ደግሞ የግድና አስፈላጊ ነው ። የሚከዱ ስለበዙ ማለት ነው ። ዛሬ ማን ያውራ ያልነበረ ሁኔታ ሰፍኗልና ደግሞ ደጋግሞ መናገሩ የግድ ሆኖ ይገኛል ። በአፍ ይቻላል እየተባለ--አባባሉ ቄንጥ ሆኗልና-- በልብ ግን አንችለውም ሰፍኖ ቡለኑ አገዛዝ አይደፍሬ መስሎ ባጅቶብናል፤ ጨፍሮብናል ። ይህን ሁኔታ ለአንዴም ለሁሌም ማስወገዱ የእኛ ግዴታም ችሎታም ነው ። ምሽግ ይፈርሳል፤ ወያኔም ይሸነፋል።

**ልናምነው የሚገባው ሀቅ ይህ ነው ።**

የሀገር ልጅ ኢሕኣፓ፡ የጥንቱ
ያዳፈኑት ኣሳት ሲገኝ ደስ ማለቱ
ምን ትጠብቃለህ ፋኖ ተሰማራ፡ ፋኖ ኣንሰማራ
መሰዋትነት ከፍለን ኣገር ለንታደግ፡ ትዉልድ ልናኮራ
ቅሌን ጨርቄን ሳልል ዞር ብዬ ቀዬዬን ሳላይ
ልሂድ ልደባልቅ ከጀግኖኖቹ አንባ፣ የሀገሬን በደሏን ስቃይዋን ላላይ
ጥንት አባቶቻችን ታግለዉ ኣቆዩን
ደግሞም ልጆቻቸዉ ኣንደንርሱ ኣንሁን
ብሔራዊ ፍቅር ኣሸንፎ ወጥቶ
የመጣዉን ጠላት በኣንድላይ መክቶ
ህገርን ኣኩርቶኣል ትዉልድ ታሪክ ሠርቶ
ጥንት ኮሎኒያሊስቶች ያጧትን ሀገር
ህንዴት በቅጥረኞች ክብሯ ይደፈር
ኣሁን የተያያዙት ሀገር ማጥፋት ሥራ፣ ትዉልድ ማጥፋት ሥራ
መዘዙ ብዙ ነዉ ኣጠፋዉ ሲመለስ በወያኔ ጎራ
ፋኖ አንሰማራ፣ ፋኖ አንሰማራ
አንደ ኣባቶቻችን ታሪክ ሠርተን አንኩራ
ፋኖ አንሰማራ፣ ፋኖ አንሰማራ

ድል ለሰፊዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ
ኣናቸንፋለን

ከመቻልበርሱ ይቻላል

ካለፈው የቀጠለ

በነሱ ጊዜ በነሱ ዘምን
ተማሪ ከተማሪ ተጠራርቶ
በመምህሩ ተኩራርቶ
መድህኒያለም ሁለትኛ ደረጃ፣ ኣርበኞችን በድንጋይ ጠርቶ
ኣርበኞችም ደወል ሣይደወል፣ ኀረፍት ወጠቶ
በኩራት መድህኒያለምን ተቀላቅሎ ድንጋይ በኪሱ ሞልቶ
ኣንደንኛ ደረጃ ነዉ ብለዉ ሳይኮሩ ሳይኩራሩ
በኣንድነት ተጓዘ፣ ቀለመወርቅን ሊጠሩ
በሃይ በትግል ነዉ ነፃነት የሚገኘዉን ሊያሳዩ፣ ሊያስተምሩ
የጀግኖችን ስም ሲጠሩ ታሪክ ሲዘክሩ

**ይቀጥላል........**

ኣንተነህ ከቶሮንቶ

ከገጽ 4 የዞረ..... 70 ጄኔራል ተብየዎች ተሾሙ

ባደረገ ሶስት ሳምንት ባልሞላ ግዜ ውስጥ የራሴ ናቸው ያላቸውን ጄኔራል መኮንኖች የማዕረግ እድገት መስጠቱ በወያኔ መከላከያ ውስጥ ትልቅ ችግር ተፈጥሮ እንደነበርና ያመላከተ እርምጃ ነው ተብሎዋል፡፡

በ1993 ዓ.ም ተፈጥሮ በነበረው በሕወሀት ክፍፍል ወቅት የወያኔ ኤታማዦር ሹሙ ጻድቃን ገብረተንሳይ ከነስዬ ጋር ወግኖዋል ተብሎ በነሳሞራ የኑስ ቡድን ሲወገዝ እና ሲብጠለጠል እንደነበረው ሁሉ ሌ/ጄ/ል ታደሰ ወረደ በዳር ፉር የሰላም አስከባሪ ኃይል መሪ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ድንገት ለስራ ትፈለጋለህ በሚል ተጠርቶ ጡረታ እንዲወጣ ከመደረጉ በላይ ዮሐንስ ገብረመስቀል ለተባለው የሌ/ጄ/ልነት ማዕረግ መሰጠቱ በወያኔ ጄኔራሎች መሀከል የተፈጠረው ትርምስ በነሳሞራ የኑስ ቡድን የበላይነት የተጠናቀቀ መሆኑን ያረጋግጣል።

ሰሞኑን የማዕረግ እድገት ከተሰጣቸው 6 ሜጄር ጄኔራሎች መሀከል አራቱ የወያኔ የበረሀ ታጋዮች ሲሆኑ የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ ኦሮሞ እና አማራ መሆናቸውም ታውቆዋል፡፡ ከሜጄር ጄኔራነት ሌላ 28 ኮሎኔሎች የብርጋዲየር ጄኔራልነት ማዕረግ የተሰጣቸው ሲሆን ከእነዚህ መኮንኖች መሀከል 19ኙ የወያኔ መኮንኖች ሲሆኑ የተቀሩት 9ኙ ደግሞ የደኢህዴን...የብአዴና የኦህዴድ መሆናቸውንም ከመከላከያ የውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በመከላከያ ውስጥ የአንድ ወገን የበላይነት ነግሶዋል እየተባለ በሰራዊቱ ጥያቄ ሲነሳና ብዙ ውዝግብ ሲፈጥር የነበረውን ጥያቄ ከማርገብ እና ፍትሀዊ ከመሆን ይልቅ የወያኔ የበላይነት ለማረጋገጥ ሲባል በአጠቃላይ ከተሾሙት 35 ጄኔራሎች መሀከል 24ቱ ጄኔራሎች የወያኔ አባላት እንዲሆኑ ተደርጓል።

የጄኔራል መኮንኖቹን ሹመት እንዲጸድቅ ‹ደረገና በመከላከያ መኮንኖች መሀከል የተፈጠረውን ሽኩቻ በበላይነት መቆጣጠሩን ካረጋገጠ በሁዋላ ሳሞራ የኑስ ሰሞኑን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቶዋል፡፡

የመከላከያ ኤታማዦር ሹሙ ሳሞራ የኑስ ሰሞኑን አጠቃላይ የጦሩን እንቅስቃሴና በጦሩ ውስጥ የነበረውን የእርስ በርስ አለመግባባት ችግር መቀረፉን አስመልክቶ በገደምዳሜ መግለጫ የሰጠ ሲሆን ዋና ትኩረቱ በበላይነት ያጠናቀቀውን የመከላከያ ጄኔራሎችን ትርምስ እንዳሸነፈ በሚያሳይ መልኩ መናገሩ ታውቆዋል፡፡

በወያኔ ቡድን ውስጥ የተፈጠረውን የእርስ በርስ ሽኩቻና ትርምስ ለማርገብ ሲባል አራት ነባር የወያኔ ባለስልጣናት በሚኒስትር ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የፖሊሲ አማካሪዎች ተብለው በቅርቡ የተሾሙ መሆናቸው የሚታወስ ሲሆን በመከላከያ ጄኔራሎችም መሀከል የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብና የአንድ ወገን የበላይነት ለማንገስ 35 ጄኔራሎችን በአዲስ መጤው ፕ/ት ተብየው ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ እንዲሾሙ ተደርጎዋል፡፡

መለስ ከሞተ ወዲህ በአንድ ዓመት ግዜ ውስጥ ብቻ ለ70 ጄኔራሎች የማዕረግ እድገት የተሰጠ ሲሆን እድሜያቸው የገፋው እነ ሳሞራ የኑስ እና ሳዓረ መኮንን በጡረታ መገለል ሲገባቸው ባሉበት ስልጣን ላይ ተቀምጠው የሀገር እና የህዝብ ሀብት እየዘረፉ ከመሆኑም በተጨማሪ ግልጽ እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ስራ እንዳይሰራ በጎጥ እና በመንደር የተከፋፈለ ....ሀገራዊ ስሜት የሌለው ....የመከላከያ ሰራዊት እንዲደራጅ እያደረጉ የሚገኙ መሆናቸውን ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ፍኖተ ዴሞክራሲ**
**የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**

**በሳምንት ሁለት ጊዜ ረቡዕና እሁድ በኢትዮጵያና በጎረቤት አገሮች ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በ25 ሜትር ባንድ አጭር ሞገድ የሚተላለፍ የራዲዮ ፕሮግራም።**

**ፕሮግራሙን በ www.finote.org መከታተል ይችላል።**

## የመምህር ወርቅዓለማሁ ንጋቱ መራር ትዝታ

ከገጽ 5 የዞረ

“አዳነ ዕምባቆም የሚባል ልጅ መለመለኝ ፤....ዴሞክራሲያን አስነበበኝ ፤........”

“ዬት ቀበሌ ነዉ ?/... ቤቱን ታሳዬናለህ?/ “ በጥድፊያ አቋረጡኝ ።

“አይ ፤ ...እርሱማ ወታደርነት ተቀጥሮ ሄዷል ።

”መልሴ በጣሙን አናደዳቸዉ ። “አሃ/...ይህቺ የኢሕአፓ ታክቲክ ናት ።....ማን አባትክን ልታታልል ነዉ ፤ አንት አናርኮ ?/” በማለት ጮሁብኝ ። ከዚያ ወዲያ ያወረዱብኝ ዱላ ወሰን አልነበረዉም ። በእጃቸዉ ፤ በእግራቸዉ ፤ በዱላ ፤ በሽጉጦቻቸዉ ሰደፎችም . . . ተረባረቡብኝ ። በመሃከሉ ከስስ ብልቴ ላይ ያረፈብኝ ምት ራሴን አስቶ ገላገለኝ ። ተጠቅልዬ ወደቅኩ ። ጎትተዉ ወደበሩ ጥግ ጣሉኝ ።ከአፍታ በኋላ በሳንቃዉ ቀዳዳዎች የሚገባዉ ቀዝቃዛ አየር ቀስቅሶ ወደ እዉነታዉ መለሰኝ ። ሰዉነቴ በላብ ኩሬ ተነክሯል ፤ ከአፍ ከአፍንጫዬም ደሜ ይፈልቃል።

በስተመጨረሻዉ ተረታሁ። በወቅቱ ኢሕአፓ ለሚያራምዳቸዉ ዓላማዎች ታላቅነትና እዉነተኛነት ከጎኑ የተሰለፍኩ ቢሆንም በድርጅቱ ዉስጥ ግን በጣም ተራ ተሳታፊ ነበርኩ ። ስቃዬን ለመቀነስ ስል ፤እንዳቅሜ ስለድርጅቱ ከማዉቀዉ ዉስጥ ልደብቀዉ የማይቻለኝንና ለወደፊቱ ለጾጸት የማይዳርገኝን የተወሰነ ሥራዬንና ግንኙነቴን በማጋለጥ አስመዘገብኩ።

በምርመራዉ ላይ በተፈጸመብኝ ኢ-ሰብዐዊ ድብደባ የተነሳ ለአንድ ቀን ሽንቴን የከለከለኝ ሲሆን በሁለተኛዉ ቀን ደም ሸንቻለሁ ። በግርፋቱ ጭኖቼና ጀርባዬ በመጎዳታቸዉ ለሁለት ዓመታት ገላዬ እየቆሰለ በማዠት ይገለፈፍ ነበር ። የእግሮቼም ጣቶች ለረዢም ጊዜ ደም ቋጥረዉ በልዘዉ ቆይተዋል ። ርግጥ ነዉ ፤ በአካሌ ላይ የደረሰዉ ሥቃይ ዉሎ አድሮ ድኗል ። ኅሊናዬ ግን ዛሬም ደም እንደቋጠረና ሕመሙ እንደተሰማዉ አለ ።




## ፍኖተ ኅብረት የኢሕአፓ ድምጽ

**በዋሽንግተንና አካባቢው ለሚኖሩ አድማጮቹ በ WTNT 730 AM የሚያስተላልፈው እስከ November 30, 2013 ድረስ ብቻ ነው። ከ November 30, 2013 በኋላ የምናስተላልፍበትን ሞገድ በ ተለያዩ መንገዶች ለሕዝብ የምንገልጽ ሲሆን በኢንተርኔት www.finote.org ላይ ወይም በስልክ 484-718-9523 በሰዓቱ በቀጥታ ማስተላለፋችንን የምንቀጥል መሆኑን እንገልጻለን።**

**የፍኖተ ሕብረት አዘጋጆችን ለመገናኘት፡**

**ስልክ 202-291-4217**

**E-mail: efdpu@aol.com**

# አገራችንን እናድን

| ኢሕአፓ ለመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ<br><br>ኢሕአፓ ለሕዝብ መብት መረጋገጥ | ኢሕአ<br>EPRP<br>For a Better Tomorrow | ኢሕአፓ በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ አንድነት<br><br>ኢሕአፓ ለሀገር ሉዓላዊነት |
|---|---|---|

## አርባ አንደኛ  ዓመት በዓላችንን ስናከብር

ፓርቲያችን ኢሕአፓ የተመሠረተበትን አርባ አንደኛ ዓመት ለማክበር አባላቱና የፓርቲ ደጋፊዎች በከፍትኛ ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዓሉ የሚከበርበት ቀን ህዳር 10 ቀን 2006 ወይም ኖቬምበር 23 ቀን 2013 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ እንዲሆን መወሰኑንም ተረድተናል፡፡ ያካባቢው ነዋሪዎች የፓርቲው ወዳጆች እና ደጋፊዎች እንዲሁም መላው ኢትዮጵያዊያን  የበአሉ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ በአክብሮት እንደተጋበዙም ታውቋል፡፡ የኢትዮጵያውያኑ በበዓሉ መገኘት ለበዓሉ ድምቀት ከመስጠትም ባሻገር፤ በዓሉ ከአንድ የፓርቲ በዓል አከባበር አልፎ ተርፎ የኢትዮጵያም በዓል እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ኢሕአፓ የተመሠረተበት ዓይነተኛ ዓላማና ግብ የኢትይጵያን ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና ሀገራዊ አንድነት ጠብቆ ለማስጠበቅ በመሆኑ፡፡

ይህንን ዓላማና ግብ ርዕይ አድርጎ የተመሠረተ ፓርቲ፤ ላለፉት አርባ አንድ የትግል ዓመታት የዘለቀው፣ ከባድና እልህ አስጨራሽ ትግል እያደረገ መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስገንዘብ አያሻውም፡፡ ምክንያቱም የፓርቲ አባላት የሕዝብ ህይወት ህይወታቸው ፤ችግሩ ችግራቸው፤ በደሉ በደላቸው፤ ጥቃቱና ቁጭቱ ቁጭታቸው፤ ተስፋና ራዕዩም ራዕያቸው በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ዕውነታ  ኢሕአፓን ለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ብቻ እንዲያስብና እንዲትከነከን አድርጎታል፡፡ ለኢትዮጵያ መቆምና ለኢትዮጵያ እየታገለ መሰዋቱ ከኢትዮጵያዊነት የተለየ ማንነት፤ ተግባርና ምግባር የሌለው መሆኑ አረጋግጦለታል፡፡ የፓርቲው ራዕይ ዓልፋና ኦሜጋ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ብቻ ነው፡፡

ይህንን ከባድ ሀላፊነት እና ግዴታን የሚጠይቅ ትግል ሲያካሂድ ተዘርዝሮ የማያልቅ ጥቃትና በደል ተደራርቦበታል፡፡ ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ጥቅም ስለታገለም የውጭ ጠላቶችና የውስጥ ባላንጣዎች ተረባርበውበታል፡፡ ባዕዳን ሀይሎችና ሀገር በቀል አጥፊዎች በአንድነት ተሰልፈውበታል፡፡ ሁሉንም እንደየአመጣጣቸው እየተፋለመ ተቋቁሟቸዋል፡፡ ይህንን የመቋቋም ሀይልና ብርታት ያገኘውም ከአይበገሬው ኢትዮጵያዊ ሰብዕናውና ባህሪው ነው፡፡ ይህ የማንነት ባህርይው ደግሞ የድርጅት ነጻነቱን ጠብቆ እንዲታገል አስችሎታል፡፡ ይህ የድርጅት ነጻነትን መስከበር ማለት ደግሞ፣ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ነጻነትና ክብር በቀናኢነት መጠበቅና ማስከበር ማለት ነው፡፡ የዚህ ሀቅ ድምር ውጤት ኢሕአፓ የውጭ ሀይሎችን ርዳታና ድጋፍ እንዳያገኝ አድርጎታል፡፡ የዚህ አይነት እርዳታ ባለማግኘቱ ግን አይቆጭም፡፡ ይህም ሲባል ፓርቲው ትብብርና አይዞህ ባይ አያስፈልገውም ማለት ሳይሆን ርዳታውና ትብብሩ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ጥቅም ላይ የማይደራደር መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል ለማለት ነው፡፡ የቆመበትን ዓላማና ራዕይ የሚፈታተን ማንኛውምን ርዳታና ትብብር ሁሉ ለመቀበል ያልተዘጋጀ ፓርቲ በመሆኑ ጅርጅታዊ ነጻነቱን አስጠብቆ ይታገላል፡፡ በዚህ  ጠንካራ መርህ ላይ የተመሠረተ አቋም በመያዙ ብቻ ባላንጣዎቹ  እና የኢትዮጵያ ጠላቶች አይንህን ላፈር ይሉታል፡፡ ለእኔ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ ከሚሉት አጥፊዎች ጋር የሞት ሽረት ትግል ሲያካሂድ የኖረውና አሁንም ቢሆን ባይበገሬነት የሚታገላቸው በዚህ ዘመንና ሀኔታ በማይለወጠው ጠንካራ አቋሙ ነው፡፡ ይህም ኢሕአፓን ኢሕአፓ ከሚያደርገው ማንነቱ ጋር ሲዳመር ከፍተኛውን የሞራል ልዕልና እንዲኖረው አድርጎታል፡፡

የመንግሥት ሥልጣን አያያዝና አካሄድ የሚመሰረተው፣ መጀመሪያ የዴሞክራሲ ሥርዓት በሀገሪቱ ሲሰፍን ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምን እና ለዚህም ስለሚታገል፣ሥልጣንን ባቋርጭ ለመያዝ ሲቋምጡ ከነበሩት እና አሁንም ከሚቋምጡት ጋር የማይስማማው ዋናው ልዮነት ይህ በመሆኑ ነው፡፡ ላለፉት አርባ አንድ ዓመታት የትግል ታሪኩ እንደሚመሰከርለት፣ ሦስቱንም ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች አጥብቆ የተፋለማቸው ዓላማው ይህ ስለሆነ እንጂ ሌላ አብነት ኖሮት አይደለም፡፡ በአንድ የዘመን ቀመር ሲሰላ፣ አርባ አንድ ዓመት የአንድ ትውልድ ዕድሜ ነው፡፡ ቀላል ዘመንም እንዳልሆነ ፓርቲው ይገነዘባል፡፡ በዚህ የትግል ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ካምባገነን ሥርዓቶች ባለመላቀቁ ፣ ፓርቲው እንደ እግር እሳት ያንገበግበዋል፤ ይቆጨዋል፡፡ ይህም በበለጠ ተጠናክሮ ትግሉን እንዲቀጥል አስችሎታል እንጂ ታከተኝ ደከመኝ ብሎ አይቦዝንም፡፡ ይህንን አይበገሬነት እንኳንስ የሚታገልለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ባላንጣዎቹም ቢሆኑ ሳይወዱ በግድ በሚገባ ይረዱታል፡፡ እንደ ብረት ቆሎ የማይቆረጠመው በህርይው መንፈሱን ይበልጥ እያጠነከረ ከመታገል በቀር ሌላ ምርጫ እንደሌለው የሚያውቅ ያውቅለታል፡፡ አርባ አንደኛ በዓሉን ሲያከብርም በትግል ሜዳ የተሰውቱን ሰማዕታት በክብር እያስታወሰ እና የተሰውበትንም ብሔራዊ ዓላማ ጠብቆ ከግቡ ለማድረስ ተጠናክሮ በይበልጥ ትግሉን ለመቀጠል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳኑን በማደስ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችን በነጻነቷ ለዘለዓለም ትኑር!
ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!

| | |
|---|---|
| ቀን፡ | November 23, 2013 |
| ቦታ፡ | 4335 16th street NW Washington, DC. 20011 |
| ሰዓት፡ | ከ 6፡00Pm ጀምሮ |